የሰ/መ/ቁ. 26422

ጥቅምት 28 ቀን 2000 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድ መሐመድ

ሐጐስ ወልዱ

መስፍን ዕቁበዮናስ

ተሻገር ገ/ስላሴ

ብርሃኑ አመነው

**አመልካች፣** ወ/ሮ ስንልሽ ማዘንጊያ - ጠበቃ ቀረበ

**ተጠሪ፣** እነ አቶ ተስፋ ማዘንጊያ - ቀርበዋል

መዝገቡን መርምረን የሚቲለውን ፍርድ ሰጥተናል፣

**ፍ ር ድ**

በዚህ ጉዳይ የአሁኖቹ ተጠሪዎች በአመልካች ላይ ኅዳር 20 ቀን 1998 ዓ.ም ባቀረቡት ክስ፣የአሁኗ አመልካች ግምቱ ብር 190,850 (የአንድ መቶ ዘጠና ሺ ስምንት መቶ ሃምሳ) የሆነና ከአውራሻችን ከወ/ሮ የንጉሤ ማዘንጊያ የሚደርሰንን የውርስ ንብረት የያዘች ስለሆነ የውርስ ንብረት ታካፍለን የሚል ነው፡፡ የአሁን አመልካች ለክሱ ከሰጠችው መልሶች መካከል፣አሁን የተጠየቀውን የውርስ ንብረት ወራሽ መሆኔ በፍ/ቤት ተረጋግጦ ላለፉት 10 ዓመታት በእጄ የቆየ ስለሆነ ተጠሪዎች በይርጋ ቀሪ የሆነን ጉዳይ አንስተው ሊጠይቁኝ አይገባም የሚል ይገኝበታል፡፡ አቤቱታ የቀረበለት የሰሜን ጎንደር መስተዳደር ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት የአሁኗን አመልካች የይርጋ ጥያቄ ውድቅ በማድረግ የውርስ ንብረቱን ከሳሽና ተከሳሾች እኩል ይካፈሉ ብሏል፡፡ ጉዳዩን በይግባኝ የቀረበለት የአ/ብ/ክ/መ/ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኙን በፍ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 337 ውድቅ በማድረግ መዝገቡን ዘግቶታል፡፡

የሰበር አቤቱታው በዚህ ላይ የቀረበ ሲሆን ፣ይህ ችሎት የካቲት 13 ቀን 1999 በዋለው ችሎት የሥር ፍ/ቤት የይርጋ ጥያቄውን ያለፈው በአግባቡ መሆን አለመሆኑን



ለመመርመር ሲባል መዝገቡ ለሰበር እንዲቀርብ ትዕዛዝ ሰጥቶ የግራ ቀኙን የቃል ክርክር ሰኔ 26 ቀን 1999 ሰምቷል፡፡

በዚህ ጉዳይ የሥር ፍ/ቤት የይርጋውን ጥያቄ ውድቅ ያደረገበት ዋነኛ ምክንያት የአሁኗ አመልካች ለክርክሩ ምክንያት የሆኑትን የውርስ ንብረቶች የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1000 /2/ በሚደነግገው መሠረት ከ15 ዓመት በላይ በይዞታዋ ስር ስላላደረገች ክሱ በይርጋ ቀሪ አይሆንም በሚል ነው፡፡

በመሠረቱ አውራሽ የተባሉት ወ/ሮ የንጉሤ ማዘንጊያ መጋቢት 7 ቀን 1988 ዓ.ም ከዚህ ዓለም በሞት የተለዩ መሆኑ ታውቋል፡፡ የአሁኗ አመልካች ግንቦት 15 ቀን 1989 ዓ.ም የሟች ሕጋዊ ወራሽ መሆኗ ተረጋግጦ ንብረቱን ይዛ ስትገለገልበት ስለመቆየቷም ከፍርድ ቤቱ ውሳኔ መረዳት ተችሏል፡፡ የአሁኖቹ ተጠሪዎች ደግሞ በዚሁ ከተማ እየኖሩ ላለፉት 10 ዓመታት በተከሳሽ የተያዙትን የውርስ ንብረቶች ሳይጠይቁ መቆየታቸው ታውቋል፡፡ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1000 /1/ መሠረት ከሳሽ መብቱንና የውርስ ንብረቶች በተከሳሹ መያዛቸውን ካወቀ ሦስት ዓመት በኋላ ስለወራሽነት ጥያቄ የሚቀርበው ክስ ተቀባይነት ለማግኘት አይችልም በሚል ተደንግጓል፡፡ የሥር ፍ/ቤት ይህን መሠረታዊ የይርጋ ሕግ ወደ ጐን በመተው ግራ ቀኙ እየተከራከሩበት ያለው የውርስ ንብረት ከዘር የወረደ ርስት እንደሆነ በመቁጠር ለጉዳዩ አግባብ ያልሆነ ሕግ ጠቅሶ የይርጋ ጥያቄውን ውድቅ ማድረጉ መሠታዊ የሕግ ስህተት ነው ብለናል፡፡

**ው ሣ ኔ**

- የተጠሪዎች የውርስ ንብረት ጥያቄ በይርጋ ቀሪ ሆኗል ብለናል፣
- የአ/ብ/ክ/መ የሰሜን ጎንደር መ/ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ሰኔ 15 ቀን 1998 ቁጥር 13047 በሆነ መዝገብ የሰጠው ውሳኔ እና የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት በፍ/ይ/መ/ቁ. 09867 በሐም 17 1998 ዓ.ም የሰጧቸው ትዕዛሁች ተሽረዋል፡፡
- የዚህን ፍ/ቤት ወጭና ኪሳራ ግራ ቀኙ ይቻቻሉ፣
- መዝገቡ ያለቀለት ስለሆነ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፣

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ቤ/ኃ